# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
# በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን



## በገጠር እና ጠረፋማ አካባቢ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ፣ሰንበት ት/ቤቶች እንዲሁም ለአብነት ት/ቤቶች የመጻሕፍት ድጋፍ ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ኘሮጀክት

በማኅበራዊ አገልግሎትና ልማት ዋና ክፍል
የቅስቀሳና የገቢ አሰባሰቢ ክፍል

ሕዳር 2001

## 1. መግቢያ

ማኅበረ ቅዱሳን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ተዋቅሮ በርካታ መንፈሳዊ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል። ማኅበሩ ከ 1992 ዓ.ም ጀምሮ ገዳማት፣አድባራት እንዲሁም የአብነት ት/ቤቶች ያሉበትን ሁኔታ በማጥናት ድጋፍ የሚያደረግ ክፍል አቋቁሟአል። ክፍሉም ድጋፍ የሚያደርጉ ምዕመናንን ፣ማኅበራትን፣ ጉባኤያትን የመሳሰሉትን በጎ አድራጊ ድርጅቶችን በማሳተፍ ገዳማት እና አድባራት እንዲሁም ለአብነት ት/ቤቶች አስቸኳይ ድጋፍ እና ለዘላቄታው እራሳቸውን የሚችሉብትን የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ይህ ክፍል እስካሁን ያከናወነው ተግባር የሚያበረታታ ቢሆንም ከችግሩን ስፋትና ድጋፍ ሚያስፈልጋቸው ገዳማት፣ አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች ብዛት አንጻር ስንመለከት «ሠራተኛው ጥቂት መከሩ ግን ብዙ ነው » የሚለውን የወንጌል ቃል ያስታውሰናል ።

በተለይም በገጠር እና ጠረፋማ አካባቢ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እና ሰንበት ት/ቤቶች በቦታው የሚገኙ ምእመናን ቁጥራቸው አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የአቅም ውስንነት ይታይባቸዋል። በአብዛኛውም በነዚህ ቦታዎች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የተጠናከረ የገንዘብ አቅምና አደረጃጀት የላቸውም። ይህም አብያተ ክርስቲያናቱ  የነዋያተ ቅዱሳት እጦት እንዲጋለጡ ሆኖል። ከዚህም በተጨማሪ አገልግሎት ለማድረግ በሚያስቸግር ሁኔታ ለቤተክርስቲያን መገልገያ የሚሆን ቅዱሳት መጻሕፍት ችግር በሰፊው አለባቸው።

በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት የሰንበት ተማሪዎች የቤተክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ ተረድተው በሃይማኖት እና በምግባር የበረቱ ለመሆን የሚያስችል ሰባኬ ወንጌል ወይም መምህር የላቸውም። መምህር እንኳን ባይገኝ ሰንበት ተማሪዎቹ መጻሕፍትን በማንበብ በሃይማኖት እና በምግባር ለመጠንከር ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖራቸውም ይህን ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚያስችሉ መጻሕፍት በቀላሉ ማግኘት አይችሉም። በዚህም የተነሳ ለመናፍቃን ትምህርቶች እንዲጋለጡ ሆነዋል። ዛሬ ዛሬ በነዚህ ቦታዎች መናፍቃን የተሳሳተ ትምህርታቸውን በሄሊኮፍተር ሳይቀር የሚበትኑበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ።

የመጻሕፍት ችግሩ በአብነት ት/ቤቶች ላይም የጎላ ሆኖ ይታያል። ለምሳሌ በማኅበረ ቅዱሳን ማኅበራዊ አገልግሎትና ልማት ዋና ክፍል በ 2000 ዓ.ም በ 14 የአብነት ት/ቤቶች ላይ ባደረገው ቅኝት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መጽሐፍ ሁሉም መምህራንና ተማሪዎች የሚያነሱት አንገብጋቢ ችግራቸው ነው። የመጻሕፍት ችግር ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠው ከሚሄዱበት  ምክንያት አንዱ እንደሆነ ለመረዳትም ተችሎል። ያለውን ችግር ታግሰው የሚማሩ ተማሪዎችም ቢሆኑ ለትምህርት መርጃነት የሚጠቀሙባቸውን መጻሕፍት የሚያገኙት በተራ ወይም በውሰት ስለሆነ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ከሚገባው በላይ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል።

ከዚህም አልፎ ተማሪዎቹ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ መጻሕፎቶችን አግኝተው ባለማንበባቸው ትምህርታቸውን ቢጨርሱ እንኳን እውቀታቸውን ውስን እንዲሆን እንዳደረጋቸው ይገልጻሉ።

የአብነት ት/ቤቶች ለማጠናከርና እና ለማቋቋም በተነደፈው መርሐ ግብር የአብነት ተማሪዎቹ ለሚማሩት ትምህርት የሚያግዝ በቂ መጻሕፍት እንዲያገኙ ማስቻል የመርሐ ግብሩ ዋና ዓላማ ነው። ለዚህም በየትምህርት ቤቶቹ ውስጥ እንደየስፋታቸው መጠን ቤተ መጻሕፍት ማቋቋም አንዱ ማስፈጸሚያ ስልት ነው። ሆኖም ካለው የገንዘብ ውስንነት የተነሣ ይህ ዕቅድ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል አጥጋቢ ሥራ አልተሰራም።

ይህንን በየቦታው የሚታየውን የመጻሕፍት ችግር በተወሰነ ደረጃ ለማቃለል « ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም » እንዲል የአበው ብሂል ወገኖቻችንን ከተለያዩ ፈተናዎች አና ከመናፍቃን ትምህርት እንዲጠበቁ የቀደመውንም መንገድ በቀላሉ እንዲገነዘቡ እና ስርዓተ ቤተክርስቲያንን በአግባቡ እንዲፈፅሙ ለማድረግ እንዲቻል መጻሕፍትን ማሰባሰብ እና መለገስ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር በመሆኑ ይህ የመጻሕፍት ማሰባሰቢያ ፕሮጀክት በማኀበረ ቅዱሳን ተዘጋጅቶ ቀርቦል።

በዚህ ፕሮጀክት የገንዘብ ግምታቸው ብር 207,744.50 የሆነ 2450 መጻሕፍት፣ ቴፕ ሪከርደር፣ መጻሕፍት መደርደሪያ እና ኮምፒውተር ለማሰባሰብ ታቅዶል። በዚህም አስቸኮይ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው 202 የገጠር አቢያተ ክርስቲያናት፣ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የአብነት ት/ቤቶች እና ሀገረ ስብከቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ።

## 2. የፕሮጀክቱ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ብሉያትን ከሐዲሳት ጋር እያስማሙ ታሪክን ከሚስጥራት ጋር እያዋሐዱ በርካታ የትምሕርተ ሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የዜማ፣ የቁጥር፣ የፍልፍስና እና የጸሎት መጻሕፍት ጽፈውና ተርጉመው አስረክበውናል። እነዚህ መጻሕፍት ለሀገራችንም ሆነ ለቤተክርስቲያናት ታላቅ ቅርስ ናቸው። በዚህም የተነሳ ዛሬ ብዙ ተመራማሪዎች እነዚህን መጻሕፍት ከሃይማኖት ትምህርት ባሻገር ለምርምር ሥራዎች ይፈልጎቸዋል።

መጻሕፍት ለጨለማ ብርሃን የመንፈሳዊ ህይወት መንገድ ናቸው ። የቀደሙችውን ሃይማኖት ለማወቅ በመንገዱም ለመጓዝ የምንችለው ቅዱሳን አባቶች አስረክበውን ባለፉት ቅዱሳት መጻሕፍት አማካኝነት ነው። ምሥጢሩን ትርጓሜውን መልዕክቱን እና ታሪኩን የምናገኘው በእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ነው ። እነዚህን መጻሕፍት አንብበን ስለ ሃይማኖት እንረዳለን፤ በቅዳሴ፣ በማኅሌትና በሰዕታት ለምስጋና ለጸሎት እንገለገልባቸዋለን።

በገጠር እና ጠረፋማ አካባቢ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እና ሰንበት ት/ቤቶች በሚደረገው የመጻሕፍት ድጋፍ ካህናት የሚሰጡትን መንፈሳዊ አገልግሎት ያቀላጠፍላቸዋል። ምእመናኑ በመናፍቃን ስሁት ትምህርት ተደናግረው እንዳይወሰዱ ይረዳቸዋል። ይልቁንም በአካባቢያቸው የተሟላ መንፈሳዊ

አገልግሎት ሲያገኙ መንፈሳዊ ጽናታቸው ይጨምራል:: የሰንበት ተማሪዎችም ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በሃይማኖት ተኮትኩተው እንዲያድጉ ትልቅ እገዛ ያደርጋል:: ከዚህም ባሻገር በአካባቢው ያሉ ወጣት ሰባኪያን ወንጌል መጻሕፍትን በማንበብ በዕወቀት እንዲጎለምሱ ያስችላቸዋል:: ከአማኒያኑ ባሻገር ያላመኑት አሳምኖ የቤተክርስቲያን ልጅ ለማድረግ ስብከተ ወንጌልን ከማጠናከር ባሻገር የተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የመጻሕፍት ልገሳው ወሳኝ ድርሻ አለው::

ከዚህም ባሻገር በአብነት ት/ቤቶች አነስተኛ ቤተ መጻሕፍት ቢቋቋም ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተገቢው ጊዜ እንዲያጠናቅቁ ይረዳቸዋል ። ከዚህም አልፎ የነገይቱ ቤተክርስቲያን አገልጋይ የሚሆኑት እነዚህ ተማሪዎች የተለያዩ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የደረሷቸውን እና የተረጎሟቸውን መጻሕፍት ለማንበብ እድሉን ስለሚያገኙ የእውቀት አድማሳቸው የሰፋ ይሆናል ።

## 3. የፕሮጀክቱ ስያሜ

ፕሮጀክቱ « አንድ መጽሐፍ ይለግሱ » በሚል ስያሜ መሪ ቃል የተቀረጸ ነው:: በርካታ ለጋሾችን ለማሳተፍ እና ማግኘትም እንዲቻል ታስቦ እያንዳንዱም ግለሰብ ሳይከብደው የአቅሙን ቢያንስ አንድ መጻሕፍ እንዲሰጥ ለማበረታታት ነው:: ለጋሾች በዋናነት ከብር 3.50 እስከ ብር 400 የሚያወጡ መጻሕፍትን ከዚህም አልፎ አንብበዎቸው ቤት ውስጥ ያስቀመጧቸውን ልዩ ልዩ መጻሕፍት እንዲለግሱ ተጋብዘዋል::

## 4. የፕሮጀክቱ ዓላማ

የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በገጠርና ጠረፋማ አካባቢ የሚገኙ ምዕመናን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ መጻሕፍት በማሟላት በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድርግ፣ በሰንበት ት/ቤቶች እና በአብነት ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ከመጻሕፍት በቂ እውቀት እንዲያገኙ በማገዝ የቤተክርስቲያን ትምህርት ጥልቅ እውቀት ያላቸው ሊቃውንትንና ፣ካህናትን ማፍራት ሲሆን ዝርዝር ዓላማውም እንደሚከተለው ነው ።

- ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት፣ ለሰንበት ት/ቤቶች እንዲሁም ለአብነት ት/ቤቶች የሚያገለግሉ መጻሕፍት መለየት፣
- በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በብዛት የማይገኙ ነገር ግን ለአገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ለምሳሌ ቅዱስ ወንጌል፣ግብረ ህማማት፣ሃይማኖተ አበው ፣ስንክሣር፣ሳዕታት ፣ተዓምረ ማርያም፣ ድርሳነ ሚካኤል ፣ድርሳነ ገብርኤል የመሳሰሉት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በጠረፋማ እና በገጠር ለሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶች የሃይማኖት ትምህርትን የሚሰጡ መጻሕፍት መጸሐፍ ቅዱስ ፣መጽሔት፣ እና የካሴት ትምህርትቶች እንዲያገኙ ማድረግ፣

- ለአብነት ት/ቤቶች በመማሪያ መጻሕፍትነት የሚያገለግሉ ለምሳሌ ድጓ፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ዚቅ፣የቅኔ መጻሕፍት፣መጻሕፍ ቅዱስ እና ሌሎች የሃይማኖት መጻሕፍት እና የካሴቶች የትምሕርቶች እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ሰባኬ ወንጌል ለሌላቸው ሰንበት ትምሕርት ቤቶች ትምሕርቶችን በቴኘ ሪከርደር ለማስተሳሳለፍ እገዛ ማድረግ፣
- በጠረፋማ አካባቢ በአዲስ ለተቋቋሙ ሀገረስብገቶችን የሚሰጡት አገልግሎት ማገዝ

## 5. በኘሮጀክቱ ተጠቃሚዎች

- የምዕመናን ቁጥር አነስተኛ በሆኑባቸው፣በመናፍቃን እንዲሁም በእስልምና የተከበቡ በአብዛኛው በጅማ፣ በወለጋ፣ በወላይታ፣ በከንባታ፣ በቦረና፣ በሲዳሞ፣ በባሌ እና በአርሲ ሀገረስብከቶች የሚገኙ 75 የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እና በእነዚህ አብያተቤተክርስቲያናት የሚገለገሉ ምእመናን፣
- በመናፍቃን እና በአክራሪ እስልምና ተጠቂ ለሆኑ እንዲሁም የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የማያገኙ 80 ሰንበት ት/ቤቶች፣ በነዚህ ቦታዎች ለሚገኙ እና በአዲስ ለተቋቋሙ 5 ሀገረስብገቶች፣
- በመጻሕፍት እጦት የተነሣ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የሚገደዱ እና ለመዋዋስ የሚቸገሩ በ 47 የአብነት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአብነት ተማሪዎች፣

## 6. የፕሮጀክቱ ታሳቢ ገቢ

- ለ 75 የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በአማካይ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 530 የሆነ ለእያንዳንዳቸው የአምስት መጻሕፍት፣
- ለ 80 ሰንበት ት/ቤቶች በአማካኝ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 300 የሆነ ለእያንዳንዳቸው 12 መጻሕፍት፣
- ለ 40 የአብነት ት/ቤቶች በአማካኝ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 600 የሆነ ለእያንዳንዳቸው 15 መጻሕፍት፣
- ለአበልቲ ኪዳነምሕረት አብነት ት/ቤት /ጅማ/ ፣ለጨጎዴ ሐና የቅኔ ማስመስከሪያ /ምዕ ጎጃም/ ፣ ለጎንደር መንበረ መንግሥት መጻሕፍት ቤት /ሰሜን ጎንደር/ ፣ለዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ትርጎሜ ቤት /ምስ ጎጃም/ ፣ለአዲስ ዓለም ማርያም አብነት ት/ቤት /ምስ ሸዋ/ ፣ ለደብረ ጽጌ ማርያም አብነት ት/ቤት /ሰሜ ሸዋ/ ፣ለቤተልሔም የዜማ ማስመስከሪያ /ደቡብ ጎንደር/

መለስተኛ ቤተመጻሕፍት ለማደራጀት ያስችል ዘንድ ለእያንዳንዳቸው በአማካይ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 1800 የሚሆኑ 45 መጻሕፍት፣

- ከላይ ለተዘረዘሩት ትምህርት ቤቶች መጻሕፍቱን በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል አነስተኛ መደርደሪያ/ሣጥን/ ግምቱ 1500 ብር የሆነ
- 20 ቴፕ ሪከርደር የአንዱ ዋጋ 750 ብር የሆነ ለተመረጡ 20 ሰንበት ት/ቤቶች እና የአብነት ት/ቤቶች ለስብከተ ወንጌል አገልግለት የሚውል
- 5 ኮምቲውተር ከነፕሪንተሩ የአንዱ ዋጋ 10000 ብር የሆነ በጠረፋማ ቦታዎች ለሚገኙ እና በአዲስ ለተቋቋሙ 5 ሀገረስብገቶች
- 500 የትምህርት ካሴቶች
- 200 መጻሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ በ85 ብር

ሰንጠረዥ- **<u>አንድ ዝርዝር ተሰብሳቢ የመጻሕፍት ዋጋ</u>**

| ተራ ቁጥር | ዝርዝር | የገንዘብ መጠን | ጠቅላላ የገንዘብ መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 75 የገጠር አብያተ ክርስቲያናት | 530.00 | 39750.00 | |
| 2 | 80 ሰንበት ት/ቤቶች | 300.00 | 24000.00 | |
| 3 | 40 የአብነት ት/ቤቶች | 600.00 | 24000.00 | |
| 4 | 7 አብነት ት/ቤቶች | 1800.00 | 12600.00 | መለስተኛ ቤተ መጻሓፍት |
| 5 | የመጻሕፍት መደርደሪያ | 1500.00 | 10500.00 | |
| 6 | 20 ቴፕ ሪከርደር | 750.00 | 15000.00 | |
| 7 | 5 ኮምቲውተር ከነፕሪንተሩ | 10000.00 | 50,000.00 | |
| 8 | 500 የትምህርት ካሴት | 10.00 | 5000.00 | |
| 9 | 200 መጻሕፍ ቅዱስ | 85.00 | 17000.00 | |
| 10 | ገቢ እንዲሆን የሚጠበቅ | | 197,850.00 | |
| | ማሰራጫ እና ሌሎች ተያያዝ ወጭዎች 5% | | **9894.50** | |
| | ጠቅላላ ገቢ እንዲሆን የሚጠበቅ | | **207,744.50** | |

## 7. መጻሕፍት እንዲለግሱ የሚሳተፉ አካላት

- 60 በመቶው ገቢ በአዲስ አበባ ከተማ ለመሰብሰብ ታሳቢ ተደረጓል:: በዚህም በአዲስ አበባ የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የግቢ ጉባኤያት፣ የሠራተኛ ጉባኤያት፣ የጽዋ ማኅበራት፣ መጻሕፍት አሳታሚ ድርጅቶች፣ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሌሎች ምዕመናን
- 33 በመቶው ገቢ በአሜሪካን አገር የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ እንዲሁም በማኅበረ ቅዱሳን የአሜሪካ፣ የአውሮፓ፣ የካናዳ እና ሌሎቹን የውጭ ማዕከላት ጨምሮ የሚሰበሰብ ይሆናል
- 7 በመቶው ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ የአገር ውስጥ ማዕከላት የሚሳተፉ ይሆናል

## 8. መጻሕፍትን ለማሰባሰብ የተመረጠው ጊዜ

- በአዲስ አበባ የሚደረገው የመጻሕፍት የማሰባሰብ ቀን ከታህሳስ 11 – 12 ቀን 2001 ዓ.ም ለሁለት ቀናት ይሆናል :: በሌሎች ቦታዎች እንዳመችነቱ የሚወሰን ይሆናል ::

## 9. መርሐ ግብሩ የሚዘጋጅበት ቦታ

- በአዲስ አበባ መርሐ ግብሩ በዋናው ማዕከል ጽ/ቤት የደረግ ይሆናል ::

## 10 የመርሐ ግብሩ ዋና ዋና ክፍሎች

መርሐ ግብሩ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይኖሩታል

- የመክፈቻ መርሐ ግብር - ቅዳሜ ጧት 3:00 ሰዓት የቤተክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በተገኙበት መርሐ ግብሩ በጸሎት ይከፈታል :: የአንድ መጽሐፍ ይለግሱ ዋና ዓላማ ይገለጻል መጻሕፍት እምነትን፣ሥርዓትን ለትውልድ ለማስተላለፍ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ ይዘከራል:: በመክፈቻው ላይ የሚገኙ አካላት መጻሕፍት እንዲለግሱ ይደረጋል፣
- መጻሕፍት መለገሻ ጊዜ - መጻሕፍት የመለገስ መርሐ ግብር ሙሉ ቅዳሜ እና እሑድ /ታህሳስ 11 እና 12 የሚከናወን ይሆናል፣በዚህ ጊዘ ተሳታፊዎች መጻሕፍት ይለግሳሉ፣ለገዳማትና አድባራት እየተደረጉ ስላሉ ድጋፎች መረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- የመዝጊያ መርሃ ግብር - እሁድ ከምሽቱ 11:30 ላይ አጠቃላይ ከለጋሾች የተገኘው ገቢ ይገለጻል በተለያዩ ሥራ ለተሳተፉ አባላት ምሥጋና ቀርቦ መርሐ ግብሩ በጸሎት ይዘጋል::

## 11 ፕሮጀክቱ አስፈሳጻሚ አካል

ይህ መርሃ ግብር ተግባራዊ የሚደረገው በማኀበራዊ አገልግለትና ልማት ዋና ክፍል የቅስቀሳና ገቢ አሰባሳቢ ክፍል ነው፡፡ነገር ግን ለተግባራዊነቱ ተጨማሪ የሰው ኃይል በማስፈለጉ ለአራት ሣምንት የሚቆይ ሦስት የተለየዩ ሥራ የሚያከናውኑ ዴስኮች ይቋቋማሉ እነዚህም፡፡

- የህትመት ፣ሥርጭትና የማስታወቂያ ዴስክ
- የአዳራሽ ዝግጅት፣ የፕሮግራም እና መስተንግዶ ዴስክ
- የመጻሕፍት፣ የገንዘብ እና የሌሎች ስጦታዎች ተቀባይ እና መዝጋቢ ዴስክ

## 12. የፕሮጀክቱ የማስፈጸሚያ ስልት

- ዝርዝር የፕሮጀክት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል
- አስፈጻሚ ዴስኮች ይቋቋማሉ፡፡
- ስለ ፕሮጀክቱ አላማ ለሚመለከታቸው አካላት ገለጻ ይደረጋል፡፡
- መጻሕፍት ሊለግሱ የሚችሉ አካላት ዝርዝር ይመዘገባል በዕለቱ እንዲሳተፉ ይጠራሉ፡፡
- የመጻሕፍት አስፈላጊነት፣ የመሰብሰቡ ዓላማ ፣መለገስ ያለባቸውን መጻሕፍት ዝርዝርና ዋጋ፡፡ ጊዜውን የሚገልጽ 5000 የጥሪ በራሪ ወረቀቶች እንዲሁም 1000 ፖስተሮች ይሰራጫሉ፡፡
- በስም ዓጽድቅ ጋዜጣ አስቀድሞ ስለ መርሃ ግብሩ አንዲታወቅ ጋዘጣዊ መግለጫ ይሰጣል፡፡
- አዲስ አበባ ከሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲሁም  ከማኀበሩ ማዕከላት ጋር በጉዳዩ ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡

## 13 አስተባባሪ አካላት

የሚከተሉት አካላት ለፕሮጀክቱ መሳካት ተሳታፊ ይሆናሉ

- የማኀበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር በቦታው ለለጋሾች መጻሕፍት በማቅረብ፡፡
- የማኀበረ ቅዱሳን ሕንፃ ግንባታ ዐብይ ኮሚቴ ቅጽር ግቢውን ለዝግጅት እንዲሆን በማስተካከል፡፡
- የአዲስ አበባ ሰንበት ት/ቤቶች የሠራተኛ ጉባኤያት ፣ግቢ ጉባኤያት ፣ማኀበራት ጥሪ በማስተላለፍ ይሳተፋሉ፡፡
- አዲስ አበባ ማዕከል ለመስተንግዶ በቂ የሰው ኃይል በመመደብ

- ሀ/ስብከቶች እና ማዕከላት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ት/ቤቶች ለይቶ መረጃ በማቅረብ ይሳተፋሉ፣

## 14. የመጻሕፍት ስርጭት ጊዜ

መጻሕፍት የሚሠራጨው ከጥር 1እስከ ነሐሴ 30/20001 ዓ.ም ይሆናል፡፡ ስርጭቱን የሚያካሂደው በማኅበራዊ አገልግሎትና ልማት ዋና ክፍል የቅዱሳት መካናት ልማት እና ተራድኦ ክፍል ሲሆን የአፈጻጸሙም ሪፖርት በየጊዜው ለለጋሾች በስምዓጽድቅ ጋዜጣ ይገለጻል፣

## 15. ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው የወጭ ዝርዝር

ሰንጠረዥ፡- <u>ሁለት ዝርዝር ወጭ</u>

| ተ.ቁ | የወጭ ርዕስ | በቁጥር | የገንዘብ መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የማስታወቂያና ቅስቀሳ በራሪ ወረቀት | 5000 | 2530.00 | |
| 2 | ፖስተር | 500 | 1550.00 | |
| 3 | ለአድራሻ ካርድ | 3000 | 1700.00 | |
| 4 | ባነር | 4 | 1000.00 | |
| 5 | የጥሪ ካርድ | 250 | 1000.00 | |
| 6 | የስልክ ካርድ | 12 | 1200.00 | |
| 7 | ለወንበር ኪራይ | 250 | 600.00 | |
| 8 | ለቦታ ዕዳትና ዝግጅት | | 200.00 | |
| 9 | ለትራንስፖርት | | 300.00 | |
| 10 | በዝግጅት ለሚሳተፉ መስተንግዶ | 100 | 1500.00 | ለሁለት ቀን ለአንድ ሰወ 15 ብር ሂሳብ |
| | ድምር | | 11580.00 | |
| | መጠባበቂያ | | 420.00 | |
| | ጠቅላላ ድምር | | **12000.00** | |

ሰንጠረዥ፡- **ሦስት የሚያስፈልጉ መጻሕፍት ዝርዝር በከፊል**

| ተራ ቁጥር | የመጻሕፍት ዝርዝር | አማካይ ዋጋ |
|---|---|---|
| 1 | መጻሕፍ ቅዱስ | 85.00 |
| 2 | ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ | 14.00 |
| 3 | ክብረ ቅዱሳን | 8.00 |
| 4 | ፍኖተ ጽድቅ | 11.00 |
| 5 | የሰ/ት/ቤቶች የአማርኛ መዝሙራት | 10.00 |
| 6 | Dandi amantii qu 2 | 6.00 |
| 7 | ዓምደ ሃይማኖት | 12.00 |
| 8 | ግብረ ገብነት | 12.00 |
| 9 | ወላዲተ አምላክ በነገረ ድህነት | 25.00 |
| 10 | ለቅዱስ ቁርባን እንድንበቃ ምንላድርግ? | 10.00 |
| 11 | ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶደክሳዊት | 15.00 |
| 12 | ትውፊትና መንፈሳዊ ሕይወት | 12.00 |
| 13 | መጽሐፈ ቅዳሴ ደብረ አባይ | 55.00 |
| 14 | መጽሐፈ ሰዓታት | 18.00 |
| 15 | ድርሳናት እና ገድላት | 25-49.00 |
| 16 | አረጋዊ መንፈሳዊ | 52.00 |
| 17 | መጽሐፈ ግጻዊ | 26.00 |
| 18 | የትንቢት መፃሕፍት | 71.00 |
| 19 | መዝሙረ ዳዊት | 35.00 |
| 20 | ሃይማኖተ አበው ግዕዝና አማርኛ | 90.00 |
| 21 | ሐዲስ ኪዳን ግዕዝና አማርኛ | 146.00 |
| 22 | ብሉይ ኪዳን መጽሐፈ ነገሥት | 80.00 |

| | | |
|---|---|---|
| 23 | ተአምረ ኢየሱስ/ማርያም | 55.00 |
| 24 | ፍኖተ ብርሃን | 15.00 |
| 25 | ፍትሐ ነገስት ትርጓሜ | 90.00 |
| 26 | መጽሐፈ ድጓ | 36-90.00 |
| 27 | የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃለት | 32.00 |
| 28 | ዝማሬ መዋስዕት | 40.00 |
| 29 | የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍት | 20.00 |
| 30 | ሥርዓተ ቅዳሴ ግብረ | 10.00 |
| 31 | መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት | 10.00 |
| 32 | የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት | 70.00 |
| 33 | የሥርዓት መጻሕፍት | 10.00 |
| 34 | መጽሐፈ ሕዝቅኤል | 60.00 |
| 35 | መጽሐፈ ግንዘት | 24.00 |
| 36 | ግብረ ሕማማት ግዕዝና አማርኛ | 310.00 |
| 37 | ስንክሳር | 220.00 |
| 38 | የቅኔ ግስና አገባብ | 25.00 |
| 39 | ኮኩሀ ሃይማኖት | 25.00 |
| 40 | ፍሬ ሊቃውንት | 12.00 |
| | | |
| 41 | የቁጥርና የቋንቋ መፃሕፍት | 25.00 |
| 42 | የትምህርት ካሴት | 10.00 |
| 43 | ቴፕ ሪከርደር | 750.00 |
| 44 | ሌሎች የሃይማኖትና ጠቅላላ እውቀት ሊሰጡ የሚችሉ መጻሕፍት | |